በሌትብሪጅ አልበርታ የምትገኝ ቤተሳይዳ ቤተክርስትያን ታሪካዊ አጀማመር፡

*“እንዲህም አለ። 'ለአንተ የከነዓንን ምድር የርስታችሁን ገመድ እሰጣለሁ'፤ ይህም የሆነው እነርሱ በቍጥር ጥቂቶች ሰዎች፥ እጅግ ጥቂቶችና ስደተኞች ሲሆኑ ነው። ከሕዝብ ወደ ሕዝብ፥ ከመንግሥታትም ወደ ሌላ ሕዝብ አለፉ።”*

--(*መዝሙር* 105፡11-13)

በዮሐንስ ወንጌል 1፡3 ላይ እንደሚለው 'ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም'። እኛም ሁሉን ላደረገው፣ አስጀምሮ ለዚህ ላበቃን፣ ገናም በብዙ ለሚረዳን ጌታ እውቅናን ሁሉ ከምስጋና ጋር እየሰጠን የእግ/ርን ታሪክ የሆነውን የዚህን ቤ/ክ ታሪክ እንደሚከተለው ለማስቀመጥ እንሞክራለን።

ጊዜው 2009 ነበር፣ በሌትብሪጅ ከተማ ይኖሩ የነበሩ ሁለት ባል እና ሚስት የመጀመሪያ ልጃቸውን ሁለተኛ ዓመት የልደት በዓል ሲያከብሩ አንድ ሐሳብ ከሌሎች ሁለት እህቶቻቸው ቀረበላቸው። ይህም አገልጋዮችን መጋበዝና የእግ/ርን ቃል በከተማው ላይ ማወጅ የሚል ነበር። በዚሁ መሰረት ሁለት አገልጋዮች ከኤድመንተን አልበርታ ይጋበዛሉ። ወንጌል ተሰበከ፣ ጌታ ተመለከ፣ ልደቱ በዚሁ ሁኔታ ተጠናቀቀ። ከዚህ በኋላ ግን፣ በተለይም በልደቱ ላይ ቃል ካገለገለው ወንድም ጋር እነዚያ ወንጌል በከተማው እንዲታወጅ ሐሳብ አቅርበው የነበሩ እህቶች አገልጋዩ ጋ በተደጋጋሚ ስልክ እየደወሉ ወደ ሌትብሪጅ መጥቶ ያለውን ጥቂት አማኞች መያዝ እንደሚችል ጥያቄ አቀረቡ። አገልጋዩ በመጀመሪያ ለነበረው ሐሳብ ብዙ ስፍራ የሰጠ አልነበረም፣ ምክንያቱ

(1). የሰው ቁጥር ከአራት ያልበለጠ ሲሆን ሁለቱ አልፎ አልፎ የሚገኙ ስለነበረ (2). አገልጋዩ በኤድመንተን ከሦስት ቤ/ክ በሙሉ ጊዜ ማገልገል እንደሚችል ጥያቄ ቀርቦለት ስለነበረ ለአራትና ለስድስት ሰው ብሎ ወደ ሌትብሪጅ መምጣት ብዙ ስላልታየው ሊያስብበት እና ሊጸልይበት ፈቃደኛ ባለመሆኑ፤ ነገር ግን ነገሩ ከእግ/ር መጥቷልና እነዚህ እህቶች በተደጋጋሚ ስልክ ደውለው ከመጠየቅ አላቋረጡም ነበር፣ ከሦስቱ ቤ/ክ የአገልግሎት ጥሪ ቢቀርብለትም በእግ/ር ፊት ቢጸልዩም ፈቃዱ እንዳልሆነ ለይተው ስላወቁ አገልግሎቱን አልተቀበሉም ነበር። ከዚህም የተነሳ እግ/ር ለአንድ ሰውም እንደሚገድደው በማመን አገልጋዩ ከባለቤቱ ጋር በመነጋገር በሌትብሪጅ ስላለው ነገር በእግ/ር ፊት በጉዳዩ መጸለይ እንደሚገባቸው ወሰኑ። ብዙም ሳይቆይ እግ/ር ለስፍራው እንደሚፈልጋቸውና እዚያ ቤ/ክን መጀመር እንዳለባቸው ተናገራቸው። በወቅቱ ግን ጥሪውን ለአገልጋዩ ቤተሰብ ያቀርቡና መጥቶ እንዲይዛቸው አስበው የነበሩ አራት አባላት ያለው አንድ ቤተሰብ ሲሆን ሁለተኛው ቤተሰብ ግን ብዙም የተሰጠ አልነበረም። ሌላው ቤ/ክ ወይም ህብረት ለመጀመር አሳሳቢ የነበረው ነገር በከተማው ሁለት ጊዜ ቤ/ክ ተጀምሮ ሳይሳካ በመቅረቱ አሁንም የሚጀመረው እንደማይቀጥል በነበሩት ሰዎች አንደበት በተደጋጋሚ የሚወራ ወሬ ነበር። ነገር ግን፣ ከጌታ በተቀበልነው ምሪት መሰረት ዘጸአት 17፡6 ላይ “እነሆ እኔ በዚያ በኮሬብ በዓለት ላይ በፊትህ እቆማለሁ፣ ዓለቱንም ትመታለህ፣ ህዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከእርሱም ውኃ ይወጣል' አለው” የሚለውን ቃል ሰጠን። በምድሪቷ ያለው ነገር እንደ ዓለት የጠነከረ ቢሆንም እግ/ር በፊታችን እንደሚሆን፣ ለህዝቡ የሚሆን ምንጭ በምድሪቷ እንደሚያፈልቅ ተናገረ። በተጨማሪም፣ ሁለት ጊዜ ተጀምሮ ባይሳካም አሁን ግን ተነስቶ የመመላለስ ጊዜ ስለሆነ ምሕረትንም በዚያ ስለሚያሳይ የቤ/ክቷንም ስም 'ቤተሳይዳ' እንደምንል አመለከተን።

በዚሁ በተቀበለው ምሪት መሰረት አገልጋዩ ከቤተሰቡ ጋር ወደ ሌትብሪጅ በመምጣት በቁጥር ስድስት የሆኑትን በመያዝ ህብረት ይጀመራል። ከአገልጋዩ ቤተሰብ ጋር ወደ ስምንት የሚሆን የአዋቂዎች ቁጥር እና ሦስት የሁለት ዓመት ህጻናት ጋር የተጀመረው ህብረት ቁጥሩ እየጨመረ በመሄዱ ከህብረት ወደ ቤተክርስቲያን ማደግ ችሏል። በመሆኑም፣ በ2012 'ቤተሳይዳ ቤ/ክ' የሚል ስያሜ በመያዝ እንደ እግ/ር ፈቃድ በእግ/ር ጊዜ በሌትብሪጅ ላይ ተመሰረተች። በአሁኑ ጊዜ አንድ ፓስተር፤ ፓስተር ዱባ ጉዮ፣ አንድ ወንጌላዊ፤ ወንጌላዊት ሰናይት ኃ/ሚካኤል፣ እንደዚሁም የቤ/ክ ሽማግሌዎችና ዲያቆናትን በተደራጀ መልኩ በመያዝ የራሷ መሰብሰቢያ አዳራሽ ኖሯት ወንጌልን በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጪ ባላት ራእይ በማሰራጨት ብዙዎችን በመድረስ ላይ ትገኛለች። እንዲሁም፣ እግ/ር በአባላት ቁጥር ያበዛት እና እያበዛት ያለ በጥሩ መንፈሳዊ እድገት ላይ የምትገኝ ቤ/ክ ናት።

ክብር ሁሉ በሰማይና በምድር ብቻውን ጌታና አምላክ ለሚሆን ለልዑል እግ/ር ይሁን። አሜን።

*“ የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፥ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን”*

--(ነህምያ 2፡20)


Every Child Matters
EXPLORE MORE


I Am Alpha and Omega, the First and the Last

